# ኮሾ ፖለቲካ

ህዳር 2002

**አብራሃም በየነ**

እርግብግብ ምላሱ- እንጀራውን አብሳይ
ትርፍ ተርፍራፊ - እይፈልግ አስመሳይ
አለሁ አለሁ ብሎ - የማታ የማታ
አመሻሹ ላይ ግን - የከዳ በጫታ
ወይ ተስፋ አይጥሉበት - ስንቅ አይሆን እምነቱ
አይታመን ቃሉ - ማተብ አልባ አንገቱ
አሉን ተቃዋሚ - የሚንሸራተቱ።
የጎተራ ነቀዝ - የዕበላ ባይ አውራ
ጆሮ ጠቢ ሰላይ - ጥላቢስ ሰዋራ
እጀጠባብ ለብሶ - አስመሳይ ሀበሻ
ለሆዱ ያደረ - የፈረንጅ ውሻ
ቀለመ ዥንጉርጉር - ቃሉ ዘለባብዳ
ብዙ ምሁር አለን - አገሩን የከዳ።
መሃንዲስ ጠበቃ ፕሮፌሰር ቢሉ
ብዙ ምሁር አለን - የወለደው ትግሉ
አለን የሰው ዓይነት - ዘማዊ ዐመሉ
አዛውንት ሸበቶ - አንተ አይሉት አንቱ
አለን ፕሮፌሰር - ሳልሳዊ ልደቱ
ትግሉ የወለደው - የአብዮቱ ውርዴ
ዶሮ ዕርባታ…ሆቴል…. - የሰው ደም ነጋዴ።
እነዚህ እነዚህ - ቅን ቅኖቹ ወተው
ለዕይታ ሲበቁ - በህዝብ ፊት ጎልተው
ሰላም ዕኩልነት -አንድነት የሚያድል
ያኔ ይጀመራል- ጥራት ያለው ትግል።

abraham beyenne